# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 113 ሐምሌ 8 ቀን 2002 ገጽ 1

**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

ግዜ

## በኡጋንዳ ዋና ከተማ ካምፓላ በደረሱት ፍንዳታዎች የሟቾች ቁጥር ጨምሯል፤ አልሻባብ ለጥቃቱ ሃላፊነትን ወስዷል

በኡጋንዳ ዋና ከተማ ካምፓላ የደረሱት ፍንዳታዎች “ኢትዮጵያን ቪሌጅ” በተባለ የኢትዮጵያውያን ምግብ ቤት እና “ረግቢ ክለብ” በሚባል ቦታ በርካቶች የአለም ዋንጫን የፍጻሜ ግጥሚያ ለማየት ተሰባስበው በነበሩ ሰዎች ላይ ሲሆን በቦታው ኡጋንዳውያን እና ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ፤ አሜሪካውያንም እንደነበሩበት ታውቋል። ጥቃቱ የተፈጸመው የእግር ኳስ ጫወታ እያዩ ለመዝናናት የተሰባሰቡት ነፍሳት ባልገመቱት ሁኔታ እንደነበርም ታውቋል። እሁድ ሃምሌ 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተከሰተው ፍንዳታ የሞቱ ሰዎች ቁጥር ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ 76 መድረሱን አለማቀፍ የዜና አውታሮች ዘግበዋል።

የሶማሊያው አልሸባብ ቡድን ለጥቃቱ ሃላፊነት መውሰዱም ተዘግቧል። አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ የተባለውን የዜና አገልግሎት ያናገሩ አንድ የአሜሪካ ባለስልጣን አልሸባብ ወንጀሉን መፈጸሙን ለማመን የሚያበቃ በቂ ምክንያት አለ ብለዋል።

ፍንዳታዎቹ የተከሰቱት የአለም ዋንጫን የመጨረሻ ግጥሚያ ለመመልከት በርካቶች በተሰበሰቡበት መሆኑን ማክሰኞ እለት መዘገባችን ይታወሳል። ከሞቱት ሰዎች ውስጥ አስራ አንዱ ከኢትዮጵያ ወይም ከኤርትራ እንደሆኑ የኡጋንዳ መንግስት መግለጹን ሲ.ኤን.ኤን የተባለው የዜና አውታር ዘግቧል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በመንግስት ሰራተኞች ላይ ህገወጥ ጫናዎችን ማድረጉን ቀጥሏል

ወያኔ ላለፉት በርካታ አመታት በመንግስት ሰራተኞች ላይ የሚያደርገው የሰብአዊ መብት ረገጣ ቀጥሎ ሰሞኑን ከስራቸው ጋር ለተያያዘ ጉዳይ የተሰበሰቡ መምህራን ያለፈቃዳቸው ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሲሰበኩ መሰንበታቸው ታውቋል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ እንደላከው ዘገባ፥ 300 የሚሆኑ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ መምህራን በማስተማር ዘዴ ላይ ስልጠና ይሰጣችኋል ተብለው በህዝብ ወጪ ለአስራ አምስት ቀናት ተሰባስበው ነበር። ነገር ግን ዘጋቢያችንን ያናገሩት የስልጠናው ተሳታፊዎች እንደገለጹት፣ ስብሰባው ተጀምሮ እስኪያልቅ የተወራው ስለ ገዢው ፓርቲ ፖለቲካ ነበር። በስብሰባው መጨረሻ ላይም ገዢውን ፓርቲ እንዲቀላቀሉ እና ለፖሊሲው ለመገዛት ቃል እንዲገቡ ተጠይቀዋል።

የወያኔ አገዛዝ በመንግስት ሰራተኞች ላይ ህገ-ወጥ ጫናን እና የሰብአዊ መብት ረገጣን በሰፊው እንደሚፈጽም እና፤ የህዝብን ገንዘብም ያለ ጠያቂ ለፓርቲ ስራ እንደሚያውል ይታወቃል። በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት ገደማ ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ቡድን መንግስት ሰራተኞች በግዴታ የፓርቲ አባላት እንዲሆኑ ስለመደረጋቸው የሚናገር ሪፖርት ማውጣቱ ይታወሳል። የአውሮፓ ህብረት የታዛቢዎች ቡድን በበኩሉ የህዝብ ገንዘብ ለፓርቲ ጥቅም ሲውል እንደነበር መስክሯል።

## በፍትህ ዘርፉ እንዲሾሙ ፓርላማ ፊት ከቀረቡ 9 ግለሰቦች 7ቱ የገዢው ፓርቲ አባላት ናቸው ተባለ

ሰሞኑን የስራ ዘመኑን በጨረሰው ፓርላማ ፊት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አባላት ሆነው እንዲመደቡ ከቀረቡት 9 ግለሰቦች ውስጥ ሰባቱ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ምሩቃን እና የገዢው ፓርቲ ሰዎች መሆናቸው ታወቀ።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ የላከው መረጃ እንደሚያስረዳው፣ አንዳንዶቹ ከዚህ ቀደም የገዢው ፓርቲ ሹመኞች የነበሩ ናቸው።

በኢትዮጵያ የፍትህ ዘርፉ በዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ሙሉ ቁጥጥር ስር እንዳለ የሚታወቅ ሲሆን፤ አንዳንድ የፖለቲካ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ዳኞች በባለስልጣናት ተጽፈው የሚላኩ ውሳኔዎችን እስከማንበብ የሚደርሱበት ጊዜ እንዳለ ከዚህ ቀደም ያቀረብናቸው ዘገባዎች አሳይተዋል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ለአምስት ሳምንታት ስርጪቱ ተቋርጦ የነበረው ኢሳት ነጻ የቴሌቪዥን ስርጪት አገልግሎት መጀመሩ ተገለጸ

በሃገራችን በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውና በተቋቋመ ባጭር ጊዜ ውስጥ በሃገር ውስጥና በውጪ ሃገራት ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ ተወዳጂነትንና አድናቆትን ያተረፈው ኢሳት ከአምስት ሳምናታት የአገልግሎት መቋረጥ በኋላ ከሃምሌ 7 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ስራ የጀመረ መሆኑን የኢሳት መስራች ቦርድ ለዝግጂት ክፍላቹን በሰጠው የስልክ መረጃ አስታውቋል።

እንደ ኢሳት የመስራች ቦርድ መረጃ አዲሱ የኢሳት ስርጪት የሚተላለፈው በ 11976 ሜጋ ሄርዝ ፍሪኩየንሲ፤ ቨርቲካል ፖላራይዜሽን፤ እንዲሁም 26 ዲግ ኢስት አልቲቲዩድ መሆኑንም ለማወቅ ቺለናል።

ኢሳት ለአምስት ሳምንታት ሊቋረጥ የቻለው አምባገነኑና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ከህዝብ ጉሮሮ እየነጠቀ ያለውን ከፍተኛ የህዝብ ገንዘብ በማፍሰስ ስርጪቱን ለማስተጓጎል ባደረገው ጥረት እንደሆነ ቦርዱ ገልጿል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአዲስ አበባ ሁለት ክፍለ ከተሞች እና በስድስት የመንግስት ተቋማት ብቻ ወደ 1 ቢሊዮን የሚጠጋ ብር መመዝበሩ ተዘገበ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ባካሄደው ምርመራ በመዲናይቱ ሁለት ክፍለ ከተሞች እና ስድስት የመንግስት ተቋማት ወደ 1 ቢሊዮን የሚጠጋ ብር መመዝበሩ እንደተደረሰበት ሪፖርተር የተባለው ለአገዛዙ ቅርብ የሆነ ጋዜጣ ዘግቧል።

ከዚህ ውስጥ 877.5 ሚሊዮን ብር የሚሆነው ገንዘብ የተመዘበረው በሶስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ብቻ መሆኑ ታውቋል። ምርመራው የተካሄደው በአራዳ እና በቂርቆስ ክፍለ ከተማዎች፤ በውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ በመንገዶች ባለስልጣን፣ እና በአራት ሌሎች ተቋማት ነው።

የውሃ ፍሳሽ ባለስልጣንን ሳያካትት፣ የአዲስ አበባ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣንን ጨምሮ በአምስት ተቋማት ላይ የተካሄደው ምርመራ በ2000 ዓም እና በ2001 953.7 ሚሊዮን ብር የተመዘበረ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 877.2 ሚሊዮን ብር የተመዘበረው በ2001 ዓም ብቻ ነው። ያለ ማስረጃ እና ያለ ጨረታ የተፈጸሙ ግዢዎች ለገንዘቡ መመዝበር ከተሰጡት ምክንያቶች ውስጥ ይገኙበታል።

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ በ2001 የበጀት አመት ለጉና ንግድ ስራዎች ኩባንያ የንብረት ግዢ ቅድሚያ ክፍያ በሚል 1.2 ሚሊዮን ብር መክፈሉን እና ይህም ሂሳብ እስከ ግንቦት 20፣ 2002 ዓም አለመወራረዱን ዘገባው ገልጿል። ጉና ንግድ ስራዎች ኩባንያ ንብረትነቱ የወያኔ በሆነው ኤፈርት ኩባንያ ስር እንደሆነ ይታወቃል።

የኦዲት ሪፖርቱ በውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን 13 ሰራተኞች 8.9 ሚሊዮን ብር ማጉደላቸውን በምርመራው ያገኘ ሲሆን፤ ይህም በተመረጡ የመስሪያ ቤቱ አካባቢዎች ካካሄደው ምርመራ ብቻ የተገኘ ነው። የኦዲት ሪፖርቱ በመስሪያ ቤቱ ላይ ሰፋ ያለ ምርመራ ቢካሄድ የምዝበራው መጠን ከፍተኛ እንደሚሆን ማስረዳቱም ታውቋል።

## በኢትዮጵያ ከፍተኛ የህዝብ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ግማሽ የሚያህሉት አስተማሪዎች የመጀመሪያ ዲግሪ ብቻ እንዳላቸው ታወቀ

በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ጥራት በከፋ ሁኔታ ዝቅ ማለቱ ሲነገር ቆይቷል። ካፒታል የተባለው የእንግሊዝኛ ጋዜጣ በዚህ ሳምንት ባወጣው ዘገባ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚገቡት የተማሪዎች ቁጥር ባለፉት አምስት አመታት ከእጥፍ በላይ ቢጨምርም፤ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪ ብቻ የያዙ እንደሆኑ ታውቋል።

ጋዜጣው ያነጋገራቸው እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲና የተማሪዎች ቁጥር የጨመረው ከትምህርት ጥራት አኳያ ዋጋ እየተከፈለ ነው ብለዋል። አገዛዙ ለይስሙላ ያህል የሚገነባቸውን ዩኒቨርሲቲዎች ብቃት ባላቸው መምህራን ለመሙላት ስለተሳነው፣ የዚሁ ጥራት የጎደለው የትምህርት ስርአት ፍሬ የሆኑ እና፤ ያውም ዝቅተኛ ውጤት ያላቸውን የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን በአስተማሪነት እየቀጠረ መቆየቱን ከዚህ ቀደም ዘግበናል።

ተቀጣሪዎቹ ምንም እንኳ የተሰጣቸውን ስራ ባግባቡ ለመከወን የተቻላቸውን ያህል ጥረት ቢያደርጉም፤ አንዳንዶቹ ከአቅማቸው በላይ እየሆነባቸው ስሞታ እንደሚያሰሙ ይነገራል። በአሁኑ ሰዓት በአገሪቱ ውስጥ የትምህርት ጥራት መውደቅ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጀምሮ የሚታይ ሲሆን፤ ህፃናት ልጆች አንዳንድ ክፍሎችን ሆን ብለው እንዲደጋግሙ ማድረግ በወላጆች ዘንድ ልማድ እየሆነ መምጣቱን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ አሳይቷል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔን "ልማታዊነት" የውሸት ፕሮፖጋንዳን ማምከን አንዱ ሥራችን ነው!!!

በአገዛዞች ተወዳጅ የሆኑት ጉልበት፣ ትዕቢትና ጉራ በተገዢዎች ልብ ውስጥ ፍርሃትን ብቻ ሳይሆን ቂምና የአመፃ ስሜትንም መትከላቸው ፈጽሞ የማይቀር ነገር ነው። በዚህም ምክንያት አገዛዞች ጉልበትንና ትዕቢትን ከማባበልና መደለል ጋር ቀላቅለው ያቀርባሉ። ይህ አገር በቀል አምባገነኖችም ሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ቅኝ ገዢዎች ሲጠቀሙበት የኖረ ዘዴ ነው። ፈረንጆች ይህን ዘዴ "ዱላና ካሮት" ብለው ይጠሩታል። ይህ መሰሪ ዘዴ እነሆ ወያኔንም ሃያ አመታት አዝልቆታል።

ይሁንና የወያኔ "ዱላና ካሮት" ከሌሎች አምባገነኖች ዱላና ካሮት የተለየ ባህሪ አለው። የወያኔ ዱላ ያው ዱላ ነው፤ የወያኔ ካሮትም "ካሮት" ተብሎ ይጠራ እንጂ ዱላ ነው። ስለሆነም እኛ ከወያኔ የምናገኘው ከሌሎች አምባገነኖች እንደሚገኘው የዱላ እና የካሮት መፈራረቅ ሳይሆን የዱላ እና የዱላ መፈራረቅ ነው።

ወያኔ በምርጫ ስም ሲፈጽመው የኖረው ዓይን ያወጣ ትዕቢትና ማንአለብኝነት ዱላ ነው። በዋና ዋና የመንግሥት ተቋማት የራሱን ሰዎች ብቻ መሰግሰጉ እና ተቋማቱ ለኢትዮጵያ ሳይሆን ለወያኔ ደህንነትና ምኞች የሚሠሩ መሆናቸው በኢትዮጵያና ሕዝቧ ላይ የተሰነዘረ ዱላ ነው። የፍትህ ተቋሙ እና ፍትህ ሆድና ጀርባ ሆነው በፍትህ ላይ መቀለድም ፍጹም ከሆነ ትዕቢት የሚመነጭ በኢትዮጵያ ላይ የተሰነዘረ ዱላ ነው። ንግዱንም እርዳታውንም መቆጣጠሩ ዱላ ነው። ንፁሃን ዜጎች መጨፍጨፋቸው፤ እስር ቤቶች በንፁሃን ዜጎች መጨናነቃቸው፤ ሕዝብ መተንፈሻ አጥቶ በሥጋት እንዲኖር መደረጉ፤ መረን የለቀቀ ዘረኝነትና ጭካኔ የአገዛዙ መታወቂያዎች ናቸው። ይህ ሁሉ ዱላ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ወራሪ ቅኝ ገዢዎች ይሉት እንደነበረው ሁሉ "ታይቶና ተሰምቶ የማይወቅ ልማትን ይዤ መጥቻለሁ። እነሆ ትምህርት፣ የጤና አገልግሎች፣ መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ" ይለናል። ይህ የወያኔ ካሮት መሆኑ ነው። ይህ "ካሮት" የተባለው ነገር ራሱ ዱላ እንደሆነ ባጭሩ እንደሚከተለው እናብራራለን።

አንደኛ፤ በአሁኑ ሰዓት የወያኔ የፕሮፖጋንዳ አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻልበት ሁኔታ ያተኮረው "ልማትን ያመጣሁ በመሆኔ የመግዛት መብት አለኝ የሚል ነው"። ይህ ምን ማለት ነው? ወያኔ ያመጣልን "ልማት" ሰብዓዊ ክብራችን ለማጣታችን የተከፈለን ካሳ ነው ማለት ነው? ይህ "ልማትን" እርም የሚያሰኝ፤ የሚዘገንን ነገር ነው። ይህ ልማት ካሮት ሳይሆን እጅግ የሚያሳምም ዱላ ነው። የሰው ሰውነቱ የሚታወቀው በመብላቱና በመልበሱ ሳይሆን ለሰውነቱ በሚሰጠው ክብር ነው። የወያኔ "ልማታዊ መንግሥት ነኝ፤ ይህም ገና ለብዙ ዘመናት የመግዛት መብት ያሰጠኛል" የሚለው ጉራ "እናንተ እንስሶች ናችሁ፤ የምትበሉትን ካቀረብኩላችሁ ይበቃችኋል። የሰጠኋችሁን ተቀብላችሁ ተገዙ" እያለን መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል። በአሁኑ ሰዓት የሚደረጉ የመብት ማስከበር ትግሎች በሙሉ "ፀረ-ልማት" ተብለው በአገዛዙ መፈረጃቸው በዚህ ምክንያት እንደሆነ ማስተዋል ይገባናል። ይህንን አዋራጅ ልማት "አንፈልግም" ማለት መቻል አለብን:: ሁላችንም በአንድ ልብ "እኛ እንስሶች አይደለንም፤ ለእለት እንጀራ ስንል መብቶቻችንን አሳልፈን አንሰጥም!!!!" ማለት መቻል ይኖርብናል ። ይህን ማለት ካልቻልን ግን በእርግጥም ለሰብዓዊ ክብር አልበቃንም ማለት ነው።

ሁለተኛውና አስገራሚው ነገር ነጋ ጠባ "ይህንንና ያንን ሰርቻለሁና ፀጥ ብላችሁ ተገዙ" እየተባልን ያለንበት ልማት የት እንዳለ ያለማወቃችን ችግር ነው። የራሳችንን ጓዳ ስንፈትሽ የተወራለትን ልማት አናገኝም። የት ስላለ ልማት ነው እየተወራ ያለው? አዎ! ወያኔ ራሱንና የራሱን ወገኖች አጥግቧል። የወያኔ ሹማምንት እና ዘመዶቻቸው ሰምተው በማያውቁት ሃብት ተንበሻብሸዋል። እነሱ ግዙፍ ሕንፃዎችን በከተሞች ውስጥ ገንብተዋል። ግና ይኸ ሁሉ ለእኛ ለድሆቹ ኢትዮጵያዊያን ምናችን ነው? ለመሆኑ እጅግ ጥቂት የሆኑ ሰዎች በልጽገው ብዙሃን መደህየታቸው ልማት ነው? የጥቂቶቹ የብልጽግና ምንጭም የኛ ድህነት ያመጣው እርዳታ፣ በአሜሪካ፣ አውሮፓና አረብ አገሮች ከሚገኙ ወገኖቻችን የሚላከው ገንዘብ፣ የመሬትና የሕፃናት ሽያጭ ገቢ መሆኑ እግምት ውስጥ ስናስገባ ወያኔ ጥፋትን "ልማት" እያለ እንደሚጠራ ግልጽ ይሆንልናል። በዚህ ሁኔታ የመጣ ልማት ካሮት ሳይሆን ዱላ ነው።

ሶስተኛው አቢይ ነጥብ ደግሞ በብዛትና በጥራት መካከል ያለው ግኑኝነት ነው። ወያኔ ብዛትን አጥብቆ የሚወድ በመሆኑ ቁጥሮችን በማፍላት ያልተመረተውን ተመረተ፤ ያልተሠራውን ተሠራ ይለናል። ይህ ብቻም አይደለም የእውነት የተመረቱት ነገሮችም ቢሆኑ ለጥራት ቁብ የሌለው በመሆኑ "ባይመረቱ ይሻለን ነበር" የሚያስብሉ ናቸው። "አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" እንደተባለው የዘመነ ወያኔ ምርት አረም የበዛበት ነው። ለምሳሌ፤ ተምረው ከኮሌጅ ተመረቁ የተባሉ ወጣቶቻችን እንደገና እንደ አዲስ መጀመር የሚኖርባቸው ደረጃ ላይ እንዲገኙ ተደርገዋል። ከሆስፒታሎችና ክሊኒኮች ድኖ የሚወጣ ሰው ማየት ብርቅ ሆኗል። መብራትና ውሃውም ወሬዓቸው እንጂ እነሱ ራሳቸው የሉም። ገጠር ቀድሞ ለም የነበረው ማሳ በይድረስ ይድረስ ግብርና ወደ ጭንጫነት እየተቀየረ ነው። የተለየ ነገር የሚታየው በመንገዶች ላይ ብቻ ነው፤ እሱም ቢሆን የልጅ ልጅ ልጅ ልጆቻችን መንገዶቹ የተሰሩበትን ዋጋ ብቻ ሳይሆን የወያኔ ባለሥልጣኖች የቀበጡበትንም ጨምረው ይከፍላሉ። በእውነት ይህ ነው ልማት የሚባለው? እንዲ ዓይነቱ ልማት ካሮት ሳይሆን ዱላ ነው።

አራተኛ፤ የወያኔ "ልማት" የብቃት ማነስ ማካካሻ ነው። በአሁኑ ሰዓት ጎልተው የሚታዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች በሙሉ "ፈጣን ልማት የፈጠራቸው ችግሮች" ተብለው እንዲታለፉ እየተደረገ ነው። የዋጋ ንረት፣ የሥራ እድሎች እጦት፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት፣ የሃኪሞች እጥረት፣ የመድሃኒት እጥረትና ውድነት፣ የውሃ እጦት፣ የመብራት መቋረጥ፣ የቴሌፎን መስመሮች መጨናነቅ፣ የመምህራን እጥረት፣ የትምህርት ክፍሎች መጣበብ፣ የማዳበርያ እጥረት፣ የዘር እህል እጦት ....ወዘተ "ፈጣን ልማት" አመጣቸው የሚባሉ ችግሮች ተዘርዝረው አያልቁም። እንዲህ ዓይነቱ ልማት ካሮት ሳይሆን ዱላ ነው።

በመጨረሻም የወያኔን ሬድዮና ቴሌቪዥንን ብቻ እየሰማ ላለ ሰው በዓለም ላይ እያደገች ያለችው አገር ኢትዮጵያ ብቻ ሊመስለው ይችላል። ነገር ግን በአለፉት አስር ዓመታት ውስጥ አብዛኞዎቹ የአፍሪካ አገሮች ከዚህ በፊት ባላደጉበት ፍጥነት እያደጉ ነው። አንዳዶች አገሮች እንደወያኔ የውሸት ሳይሆን የእውነት ከአስር በመቶ በላይ አድገዋል። ታድያ ዓይንን ጨፍኖ፤ ጆሮን አደንቁሮ፤ አዕምሮን አደንዝዞ በተፈጠረ ልብ ወለድ ልማት መጨፈር ብልህነት ነው ወይስ ድንቁርና። እንዲህ ዓይነቱ አደንዛዥ ልማት ካሮት ሳይሆን ዱላ ነው።

አምባገነኖች ዱላና ካሮትን ማፈራረቃቸው የተለመደ ነው። እናም አንዳዶች "ካሮቱ በርከት ካለ ዱላውን እንቻለው" እንደሚሉ እናውቃለን። ደቡብ ኮሪያን፣ ቺሊና ቻይናን እየጠቀሱ የሚከራከሩ አሉ። እነዚህ ወገኖች ያልተገነዘቡት ወይም ሊገነዘቡ ያልፈለጉት ሃቅ ግን ወያኔ ዱላና ካሮት ሳይሆን ዱላና ዱላን የሚያፈራርቅ መሆኑን ነው።

ወያኔ በልማት ስም የሚያደርስብንን የፕሮፖጋንዳ ጥቃት ለማምከን ወደፊት ገና ብዙ የምንለው ይኖረናል። ለጊዜው የሚከተሉትን አራት ነጥቦችን አጽንዖት መስጠት እንፈልጋለን።

1. ልማት ማምጣት ሕዝብን የመግዛት መብት አይሰጥም። እንዲህ ዓይነቱን የቅኝ ገዢዎች አስተሳሰብን አጥብቀን እንዋጋለን፤
2. የወያኔ ባለስልጣኖችና ዘመዶቻቸው መከበርና የፎቆቻቸው መብዛት የኢትዮጵያን እድገት አያመለክትም። ይልቁንስ ጥቂቶች የአገራችንን ሃብት ምንኛ እየቦጠቦጡ መሆኑ ማሳያዎቻችን ናቸው።
3. ለቁጥር ብዛት ብቻ በሚደረግ የይድረስ ይድረስ ሥራ በልጆቻችን ትምህርት፣ በጤናችን፣ በአፈራችን እና በዘወትር ሕይወታችን ላይ የሚሰራውን ወንጀል ማስቆም ይገባናል።

በመረጃ እጦት ታፍነን የወያኔን የልማት ቱልቱላ ብቻ የምንሰማበት ዘመን መብቃት ይኖርበታል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### በኡጋንዳ ዋና ከተማ ካምፓላ በደረሱት ፍንዳታዎች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተያያዘ ዜናም፥ የካምፓላ ፖሊስ መርማሪዎች ማክሰኞ እለት በአንድ የዳንስ ክለብ ውስጥ ያገኙት የአጥፍቶ ጠፊዎች ሰደሪያ (ማለትም ቦምብ የሚሰገሰግበት ሰደሪያ)፣ ሶስተኛ ጥቃት ታቅዶ እንደነበረ ያሳያል ማለታቸውን አሶሲየትድ ፕሬስ ዘግቧል።

ጥቃቱን ፈጽሜያለሁ ያለው የሶማሊያ ቡድን አልሸባብ፣ ወያኔ ከሶስት አመታት በፊት ሶማሊያን በወረረበት ጊዜ ተራ የወጣቶች የትጥቅ ቡድን እንደነበረ ይታወሳል። የወያኔ ወረራ በሶማሊዎች ዘንድ የፈጠረው ብሔራዊ ስሜት ለቡድኑ ጥንካሬን ሰጥቶት በአሁኑ ጊዜ በሶማሊያ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያለው ቡድን እንዲሆን እንደረዳው ይታወቃል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነት ክፍል ለዝግጅት ክፍላችን በላከው መልክት ንቅናቄው በዚህ ጥቃት በደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ሃዘን እንደተሰማው እና ለቆሰሉት ፈጣን ፈውስን፤ ለሟቾቹ ወዳጆች እና ዘመዶችም መጽናናትን እና ጽናትን እንደሚመኝ ገልጿል።

### ለአምስት ሳምንታት ስርጨቱ ተቋርጦ የነበረው . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ከህዝብ የዘረፈውንና ከዓለም አቀፉም ህብረተሰብ በሃገራችን ረሃብተኞችና በልማት ስም እየተቀበለ ያለውን እጂግ በርካታ ገንዘብ ለአፈና ያውለው እንጂ የኢሳት መስራች ቦርድ ይህንን የወያኔ አፈና በመቋቋም ስርጨቱን እንደገና በአየር ላይ እንዲውል ከፍተኛ የሆነ ጥረት ሲያደርግ እንደቆየ ለማወቅ ተቺሏል።

መስራች ቦርዱ ወደፊትም የኢትዮጵያ ህዝብ ስለሃገሩም ሆነ ስለሌላው ዓለም ትክክለኛ የሆነ መረጃ የማግኘት እድሉን ለመጠበቅ ሲባል የወያኔን አፈና በመቋቋም ያልተቋረጠ የስርጨት አገልግሎት ለመስጠት ቃል የገባ መሆኑን ገልጾ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ከጎኑ እንዲሰለፉ ጥሪውን አቅርቧል።

**በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን**

**የፖስታሳጥን ቁጥር ፡-** POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# እየደመቀ የመጣው የሕዝብ የተባበሩ እሪታና ሊሰጠው የሚገባ ምላሽ

**በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ የተዘጋጀ: ሐምሌ 2002 (ክፍል 2)**

ይህ ችግር ውብስብስ በመሆኑ ቀላል መፍትሄ የለውም። የነፃነት ታጋዮች ከግል የጥቅም ፍላጎት እርቀው ለዓላማ የመቆምን መንፈሳዊ ጽናት ሲኖራቸው ብቻ ነው ይህን ምድራዊ ፈተናን መቋቋም የሚችሉት። የርዕዮት-ዓለም ጥቅሙ እዚህ ጋ ነው። ይህንን ፈተና ሊቋቋም የሚችል ምን ዓይነት ርዕዮተ ዓለም ሊኖረን ይገባል የሚለው ጉዳይ በጥልቀት ሊታሰብበት ይገባል።

ለሁሉም የትብብር ችግሮች መፍትሄ ማመንጨት ባንችልም ቢያንስ የችግሩን ጥልቀት አውቀን መነሳታችን ቀድሞ በገባንባቸው ጉድጓዶች ውስጥ ደግመን እንዳንገባ ያግዙናል።

## 3. የድርጅቶች ጥምረትም (coalition) ደግሞ ራሱን የቻለ ሌላ ጥበብ ነው

ጥምረት የየራሳቸው ዓላማና ግብ ያላቸው የተለያዩ ቡድኖች በሚግባቡባቸው ጉዳዮች ላይ የሚሠሯቸውን ተግባራት ለማስተባበር የቆመ የቡድኖች ኅብረት ነው።

የቡድኖች ኅብረት የሚፈልገው በአንድ ቡድን ብቻ ሊሰሩ የማይችሉ ቢሰሩም ጥራታቸውና ተፈላጊነታቸው የሚጓደል ሥራዎች ስላሉ ነው። ስለሆነም ስለድርጅቶች ጥምረት ከመታሰቡ በፊት ጥምረቱ ያመጣዋል ተብሎ የሚገመተው ውጤት በአንድ ድርጅት ብቻ መምጣት የማይችል መሆኑን፤ ቢመጣም ተቀባይነቱ አነስተኛ መሆኑ በሁሉም ተጣማሪ ድርጅቶች ዘንድ የጋራ ግንዛቤ ሲኖር ነው።

የድርጅቶች መጣመር በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት።

- ጥምረት ኃይልን ይገነባል፤ "ድር ቢያብር አንበሳን ያስር" እንዲሉ በየግላቸው ደካማ የሆኑ ቡድኖች ሲተጋገዙ ይጠነክራሉ። ይህ ምናልባትም ከሁሉም በላይ ግልጽ የሆነ የጥምረት ጠቀሜታ ይመስለናል።
- የድርጅቶች መጣመር ደጋፊን ያበዛል። ተጣማሪ ድርጅቶች በየግላቸው ያልማረኩት የኅብረተሰብ ክፍል በጥምረታቸው ሊማረክ ይችላል። በዚህም ምክንያት የድርጅቶች ጥምረት ተጣማሪዎቹ ድርጅቶች በግልም በጋራም ያላቸው ሕዝባዊ ተቀባይነት /legitimacy/ ከቀድሞው እጅጉ የላቀ እንዲሆን ያደርጋል።
- ጥምረት በጥሩ ማኔጅመንት ከታገዘ ጊዜን፣ ሰውን፣ ገንዘብን፣ እውቀትን፣ መረጃን፣ እና ኔትዎርክን በተሻለ ስልጠት /efficiency/ ለመጠቀም ያስችላል።
- በጥምረት ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ለሁኔታዎችና ክስተቶች የሚሰጡት ትርጉም እንደየድርጅቶቻቸው እይታ የተለያየ በመሆኑ አንድን ጉዳይ ከተለያዩ አቅጫዎች የመመልከት እድልን ያሰፋል።

የእነዚህና መሰል ጠቀሜታዎች መኖር ነው ድርጅቶች በየግላቸው ተሯሩጠው ከሚያመጡት ድል ድምር በላይ በጋራ ሲሆኑ ይመጣል የሚባለው። እንደ አገራችን ያለ በበርካታ ችግሮች ለተተበተበች አገር የጥምረት ጠቀሜታ ከዚህም በላይ ነው። ሎሚና ብርቱካንን መደመር እንደማይቻል ሁሉ የአንዱ ፓርቲ ድል ከሌላው ፓርቲ ድል ጋር የማይደማመሩ ሁለት ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም የጋራ የሆነ ነገር (ለምሳሌ ስፐሪስ ጭማቂ) ላይ መስማማት ያስፈልጋል። ጥምረት ይህንን ወሳኝ የሆነውን ስምምነት መፍጠሪያ መድረክ ሆኖ ያገለግላል።

ይሁን እንጂ አጓጊ ጠቀሜታዎችን በማየት የድርጅቶች ጥምረት በችኮላ የሚደረግ መሆን የለበትም። ጥምረት የታወቁ ጉዳቶችም አሉት። ከሁሉ አስቀድሞ ጥምረት ድርጅቶች ከለመዱት አሰራር ስለሚያወጣቸው ውዥንብርና መደነጋገር የሚፈጥር መሆኑ ታውቆ ቅድሚያ ዝግጅት ሊደረግበት ይገባል። በዚህ ረገድ በቂ የሆነ ቅድመ ዝግጅት ካልተደረገለት የመጣመር ሙከራ ራሱ የቅራኔ ምንጭ ሊሆን ይችላል። በጠንካራ መሰረት ላይ ያልተገነባን ጥምረት ማቆየት ራሱን የቻለ ሥራ ይሆንና ሌሎች ሥራዎችን ያዘናጋል። ተጣምረው በተፋለሱ ድርጅቶች መካከል የሚኖረው ቅራኔ ከመጣመራቸው በፊት ከነበረው የባሰ ሊሆን ይችላል። ይህ በቅርብ ጊዜ ታሪካችን ውስጥ ያየነው ጉዳይ ነው። የጥምረቱ ድርጅታዊ መዋቅር በጥንቃቄ ካልተዘጋጀ ሥራዎችን በማፋጠን ፋንታ ሊያጓትት፤ ግብዓቶችን ቆጥቦ በመጠቀም ፋንታ ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል። በሁሉም የጋራ ሥራዎች ላይ ያለ "ልፋት ለሱ፤ ጥቅም የጋራ" ዓይነቱ የብልጣ ብልጥነት መርሆ በድርጅቶችም ላይ ያለ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም በጥምረት ውስጥ ያሉት ድርጅቶች ሁሉ እኩል ከልባቸው የአቅማቸውን ያህል ይሳተፋሉ ብሎ መነሳት የዋህነት ሊሆን ይችላል። ሁሉም ድርጅቶች እኩል ስለማይሳተፉ የአንዳንድ ድርጅቶች ሚና ከሌሎቹ ከፍ ሊል የሚችል መሆኑ ከመነሻው ሊታወቅ ይገባል።

ስለሆነም ጥምረት በሚገባ ተጠንቶ ደረጃ በደረጃ የሚደራጅ እንጂ ለመተባበር ወይም "አብረን ነን" ለማለት ብቻ የሚፈጠር ተቋም አለመሆኑ መረዳት እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው ብለን እናምናለን።

### 3.1 የጥምረት ተግዳሮቶች

የጋራ ዓላማ ያላቸው ድርጅቶች በመተጋገዝ ፋንታ ሲጎነታተሉ ማየት አዲስ ነገር አይደለም። ሽሪኮች ሊሆኑ ይገቡ የነበሩ ድርጅቶች ባላንጣዎች ሲሆኑ ጉዳቱ ጥልቅና ሰፊ ነው። ስለሆነም ለጥምረት የሚደረገው ጉዞ መጀመር ያለበት ባላንጣነትን ወይም መጎነታተልን በማስቀረት ነው። የወዳጅ-ባላንጣ በብዙ ምክንያቶች ሊፈጠር ይችላል፤ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1. ግቦቻችን የተለያዩ ናቸው ከሚል የተሳሳተ ግንዛቤ፤
2. የራስን ድርጅት "ግዛት" የመጠበቅ ፍላጎት - ሌሎች ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ድርጅቶች ደጋፊዎቼን ይወስዱብኛል የሚለው ስጋት፤
3. በራስ ድርጅት ውስጥ የተያዘ ሥልጣን በጥምረቱ ውስጥ አይገኝ ይሆናል የሚል ሥጋት፤ እና
4. በመሪዎች የግል የስብዕና ችግር - አንዳንድ የፓለቲካ መሪዎች እነሱ የማይመሩት ድርጅት እንዲኖር ፍላጎታቸው አይደለም።

በወዳጅ ድርጅቶች መካከል ያለው ባላንጣነት ለማስወገድ የስኬታማ ተግባቦት (effective communication) ክህሎቶችን ማዳበር ግድ ይላል። ከስኬታማ ተግባቦት ክህሎት ዋነኛው ደግሞ ከልብ ማዳመጥ መቻል ነው። ድርጅቶች በባላንጣነት የሚያዩዋቸውን ወዳጆቻቸውን ከልብ ማዳመጥን መልመድ ይኖርባቸዋል። ከልብ ለማዳመጥ ደግሞ በሌላኛው ድርጅት ዓላማዎች ላይ ፍላጎት ማሳደር ግድ ይላል። ግድየለሽ ተኩኖ ከልብ ማዳመጥ አይቻልም። ሌላው የመደራደር ፈቃደኝነት ነው። ድርድር ደግሞ በማግኘት ስሜት ብቻ አይደረግም። በድርድር አንድን ነገር ለማግኘት ሌላ ነገር ማጣትን ሊኖር እንደሚችል ማመን ያስፈልጋል። መልካም ድርድር ከመስጠትና መቀበል አልፎ የተሻለ ጎዳና ለማግኘት መጣርን ያካትታል። "ይህ ያንተ መንገድ አይደለም፤ የኔ መንገድም አይደለም። ለሁለታችንም የተሻለ ጎዳና ነው" ዓይነት ውጤት ነው የተሳካ የድርድር ውጤት የሚባለው። የምናልመው ጥምረት እንዲህ ዓይነቱ የተሻለ ጎዳና ላይ የሚያስቀምጠን ሊሆን ይገባል።

### 3.2 የጥምረት ዓይነቶች

የጥምረት ዓይነቶች በርካታ ሲሆኑ ሶስቱን ከዚህ በታች እናያለን።

1. ድጋፍ ሰጭነት/Endorsement/
   - ⇒ ድርጅቶች ድጋፍ ለመሰጣጠት የሚያደርጉት ልል ጥምረት ነው
   - ⇒ ከድጋፍ ያለፈ እምብዛም የሚያደርጉት የለም
   - ⇒ ከመግባቢያ ሰነድ ያለፈ ስምምነትም ላይኖራቸው ይችላል
2. ዝምድና /ተዛማጅ/Associate/
   - ⇒ አባል ድርጅቶች ህያው የሆነ የጋራ ተሳትፎ ያደርጋሉ
   - ⇒ ሥራዎች ቢቀናጁም ውሳኔዎች ግን የግል ናቸው
   - ⇒ በዚህ ደረጃ ላይ የጥምረቱን ሥራዎች የሚያስተባብር ከአባል ድርጅቶች የተወጣጣ አካል እና ይህ አካል የሚተዳደርበት ቢጋር /terms of refernce/ ይኖረዋል።
3. ሽርክና /Partner/
   - ⇒ ውሳኔዎች የጋራ ናቸው። የጥምረቱ ውሳኔዎች በአባል ድርጅቶች ውሳኔ ላይ የበላይነት አላቸው።
   - ⇒ ሽርክናው ራሱን የቻለ ድርጅት ሆኖ በመቋቋም የድርጅቶች ጃንጥላ ሆኖ፤ የራሱን መዋቅር ዘርግቶ ይንቀሳቀሳል። አንዳንድ የሥራ ዘርፎች (ለምሳሌ ራስን የመከላከል ሥራ፣ የውጭ ግኑኝነት፣ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች) ሙሉ በሙሉ ለሽርክናው ሊተው ይችላሉ።

የትኛው የጥምረት ዓይነት ይሻላል የሚለው ጥያቄ የሚወሰነው ለሚከተሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች በሚሰጥ ምላሽ ነው።

ሀ) አባል ድርጅቶች ምን እንዲያደርጉ ነው የሚጠየቁት?
ለ) እያንዳንዱ አባል ድርጅት ከጥምረቱ ምን እና እንዴት ይጠቀማል?
ሐ) የእያንዳንዱ አባል ድርጅትና አቅምና ዝግጁነት ምን ያህል ነው?

ሁሉም ድርጅቶች በእኩል ደረጃ ላይ ሊገኙ ስለማይችሉ ሶስቱንም የጥምረት ዓይነቶች እንደሁኔታው የምናስተናግድበትን ብልሃት መፍጠር ይኖርብናል።

## 4. በሌሎች አገራት ከነበሩ ኅብረቶችና ጥምረቶች ምን እንማራለን?

በታሪክ ውስጥ የሚጠቀሱ አንዳንድ ትብብሮችና ጥምረቶች ለማመን የሚቸግሩ ውጤቶችን አስገኝተዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች በመሣሪያ ሊገኝ ከሚችል ድል በላይ በተቃዋሚ ድርጅቶች ተባብሮ መቆም ብቻ ሊገኝ ይችላል። ለምሳሌ ያህል የምከተሉትን ማንሳት ይቻላል።

4.1 በእንግሊዝ በ1688-1689፤ በስዊድን በ1909 በፍላጎትም በርዕዮተ-ዓለምም የማይቀራረቡ የመሳፍንትና የቡርዧ ቡድኖች ተደራድረው በፈረንሳይ የፈነዳውን ዓይነት ማኅበራዊ ነውጥ ሳያስፈልግ ለሥርዓት ለውጥ በቅተዋል።

(ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)

## ፔትሮናስ የነዳጅ ቁፋሮ ቡድን ከኦጋዴን እየወጣ መሆኑ ተጠቆመ

በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የማእድን ሚኒስቴር ፔትሮናስ የተባለው የማሌዢያ ኩባንያ ከኢትዮጵያ ጋዝ ወደ ውጪ መላክ ሊጀምር አምስት አመታት ይቀሩታል ባለን በአስር ቀናት ውስጥ ለአገዛዙ ቅርብ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ድርጅቱ ኦጋዴንን ለቆ እየወጣ መሆኑን ዘግቧል።

የፔትሮናስ ሰራተኞች ከዚህ በኋላ ለስድስት ወራት ብቻ እንደሚሰሩ በድርጅቱ እንደተነገራቸው ለጋዜጣው ነግረዋል። ሪፖርተር፥ በኦጋዴን አካባቢ ያለው የጸጥታ ችግር ለኩባንያው መውጣት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ጥርጣሬ እንዳለም ገልጿል። የማእድን ሚኒስቴር ሹመኛ የፔትሮናስን የመውጣት ዜና የሃሰት ወሬ ሲል አጣጥሎታል።

የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ወይም ኦብነግ በአካባቢው ለሚቀንሳቀሱ የውጭ ኩባንያዎች ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያዎችን ማስተላለፉ ይታወሳል። ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔው አገዛዝ ኦብነግን ከአካባቢው በማጥፋት ስም ወደ ኦጋዴን ጦር በመላክ የጦር ወንጀል እስከመፈጸም የደረሰ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት መፈጸሙን አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች መናገራቸው ይታወቃል።

አገዛዙ ኦብነግ ከአካባቢው ፈጽሞ ጠፍቷል በሚልበት ወቅት እንደ ፔትሮናስ ያለ ኩባንያ ከጸጥታ ችግር የተነሳ አካባቢውን ቢለቅ እንደ ከፍተኛ ሽንፈት እንደሚቆጠርበት የዝግጅት ክፍላችን ያናገራቸው የፖለቲካ ተንታኝ ገልጸዋል።

## የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአለም ላይ ዝግ ከሆኑት ተርታ እንደሚመደብ የአለም ባንክ አስታወቀ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአለም ላይ ዝግ ከሆኑት ተርታ ይመደባል ሲል የአለም ባንክ ባወጣው ሪፖርት አስታወቀ።

አለምአቀፉ ተቋም ሰሞኑን ይፋ ባደረገው ጽሁፍ፣ ጥናት ከተካሄደባቸው 87 አገራት ውስጥ ኢትዮጵያ፣ በተለይም በአገልግሎት የንግድ ዘርፍ፣ የውጭ ኢንቨስትመንት እንዳይኖር ከፍተኛ እገዳ ከሚያደርጉት ተርታ ነች ብሏል። በተለይም እንደ ቴሌኩሚኒኬሽን እና የመገናኛ ብዙሃን ባሉት ኢንዱስትሪዎች የውጭ ኢንቬስትመንት አለመፈቀዱን ጠቅሶ፤ አብዛኞቹ ለውጭ ኢንቨስትመንት ዝግ የሆኑ ኢንዱስትሪዎች ለኢትዮጵያውያን ነጋዴዎችም እንደማይፈቀዱ እና በመንግስት ቁጥጥር ስር እንደሆኑ ገልጿል።

በቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ፣ የወያኔ አገዛዝ ከውጭም ሆነ ከአገር ውስጥ ምንም አይነት ኢንቨስትመንት እንደማይፈቅድ ይታወቃል። የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከዚህ ቀደም የተንቀሳቃሽ ስልኩን ኢንዱስትሪ እንደ ሌላ የአፍሪካ አገሮች ለግል ኢንቨስተሮች ለምን ክፍት እንደማያደርግ ሲገልጽ፤ የተንቀሳቃሽ ስልክ ንግድ ፈቃድ መስጠት ገንዘብ የማተም ፈቃድ ከመስጠት ጋር እንደሚተካከል መናገሩ ይታወሳል።

ይህ የአገዛዙ ፖሊሲ ኢትዮጵያን በመገናኛ እና መረጃ ቴክኖሎጂ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ወደ ኋላ እንዳስቀራት ይታወቃል። በአሁኑ ሰዓት በአገሪቱ ውስጥ ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት አቅርቦት ስፋትም 0.4% ብቻ ነው። የወያኔው አገዛዝ ይህን ኢንዱስትሪ አንቆ የያዘው ከንግድ ዘርፉ የሚገኘውን ትርፍ ለመቆጣጠር እና በዜጎች ላይ የሚያካሄደውን ስለላም ለመቀጠል ነው ሲሉ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ።

### በፍትህ ዘርፉ እንዲሾሙ ፓርላማ ፊት ከቀረቡ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ለምሳሌ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት የነበረው እና በፍርድ ቤቱ የመለስ ተወካይ እንደሆነ የሚነገርለት መንበረጻሃይ ታደሰ ከፖለቲካ እና ከወያኔ የንግድ እንቅስቃሴዎች ጋር ለተያያዙ የፍርድ ሂደቶች ከዳኞች በስተጀርባ ሆኖ ውሳኔዎችን እንደሚያስተላልፍ መዘገባችን ይታወሳል።

ዘጋቢያችን አዲሶቹን ሹመኞች አስመልክቶ ያናገራቸው ዜጎች፣ የገዢው ፓርቲ አባላት የፍትህ ዘርፉን እንደተቆጣጠሩት እንደሚቀጥሉ ከማመልከቱ በስተቀር በጉዳዩ አዲስ ነገር እንዳላዩበት እና እንደማይጠብቁም ገልጸዋል።

### በኢትዮጵያ ከፍተኛ የህዝብ የትምህርት ተቋማት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ባለፈው ወር አዲስ ነገር ኦንላይን በተባለው የዜና ድረ-ገጽ ላይ የወጣ ጽሁፍ "የማህበራዊ ጥናት መድረክ" ያሳተመውን መጽሃፍ ጠቅሶ፤ በ1999 ዓም አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ብሔራዊ ፈተና ከወሰዱት ተማሪዎች ውስጥ 92.4 በመቶ፤ እንዲሁም በ2000 ዓም 97 በመቶ የሚሆኑት መውደቃቸውን ገልጿል። በተጨማሪም፥ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እየገቡ ካሉት አብዛኞቹ ተማሪዎች የመግቢያ ፈተናውን የወደቁ እንደሆኑ ታውቋል።

## ግንቦት 7 ንቅናቄ ምእራባውያን መንግስታት በወያኔ አገዛዝ ላይ ጫና እንዲያደርጉ ጥሪ አቀረበ

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባወጣው መግለጫ ምእራባውያን፣ በተለይም የአሜሪካው የኦባማ አስተዳደር፣ ለጥቅማቸው ሲሉ በኢትዮጵያ በዴሞክራሲያዊ ተቋማት ላይ የተመሰረተን አዲስ ስርአት መቋቋም እንዲደግፉ ጥሪ አቅርቧል።

"ቀጣፊውን አገዛዝ በስሙ መጥራት" በሚል ርእስ በወጣው በዚህ መግለጫ፣ ከሁለት ወራት በፊት ፕሬዚደንት ኦባማ የወያኔውን አገዛዝ በአለም የነፃው ሚድያ ጠላቶች ጎን በማሰለፍ ማውገዛቸውን አስታውሶ፤ የአሜሪካ ድምጽ ራድዮ፣ የዶቼ-ቬሌ ራድዮ እና አዲሱ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ስርጭቶች መታፈናቸው ፕሬዘደንቱ ለተናገሩት ማረጋገጫ ነው ብሏል። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ሃላፊ ወ/ሮ ሂላሪ ክሊንተንም ባለፈው ሳምንት የወያኔውን አገዛዝ በአለም ላይ የሲቪል ማህበረሰቡን እየረገጡ ካሉት ተርታ ማሰለፋቸውን አስታውሷል።

ንቅናቄው በዚህ መግለጫ፣ የኦባማ አስተዳደር በአሁኑ ሰዓት ተቀባይነትን ካጣው እና በመረጋጋት ስም ከአምባገነናዊ አገዛዞች ጋር መስራትን ከሚፈቅደው የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ፖሊሲ ፊቱን እንዲያዞር እና በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ጫና እንዲያደርግ ጥሪ አቅርቧል። የኢትዮጵያ ህዝብ የሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት በሚከበርበት ነፃና ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ የመኖር ፍላጎቱ ሊከበር እንደሚገባ፤ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት እና "ኩሚኒቲ ኦፍ ዴሞክራሲስ" የተባሉት የዴሞክራሲያዊ አገራት ማህበር፣ ግልጽ እና ጠንካራ የሆነ መልክት ሊያስተላልፉ ይገባል ብሏል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ እና መሪዎቹ በአብዛኛው ዜጋ ዘንድ ፈጽሞ ተአማኒነት የላቸውም ተባለ

አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ዘረኛውን እና አምባገነናዊውን የወያኔ አገዛዝ እና መሪዎቹን በማንኛውም ጉዳይ ላይ ፈጽመው የማያምኑበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ዘገባ አሳይቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ የዝግጅት ክፍል፣ ግልጽ የሆነ ጥናት ማካሄድ ያለውን አደጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት በሶስት የተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ አገራት የሚኖሩ ዜጎችን ሳይንሳዊ ያልሆነ ሰርቬይ ወይም አሰሳ እንዲያደርጉ ጠይቆ ነበር። ሶስቱም ዜጎች ለዝግጅት ክፍላችን የላኳቸው የተለያዩ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት ከተጠያቂዎቹ ውስጥ በአማካይ ወደ 90% የሚሆኑት አገዛዙን እና ባለስልጣናቱን አያምኑም። የተቀሩት ተጠያቂዎች ጠያቂዎቹን ባለማመን እና በሌሎች ምክንያቶች መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም።

የአሰሳው ተሳታፊዎች ከተጠየቋቸው ጥያቄዎች ውስጥ፥ "አገዛዙ በየአመቱ የሁለት ዲጂት የኢኮኖሚ እድገት እየተመዘገበ ነው ይላል፤ ይህን ታምናለህ?"፤ "ባለስልጣናት በተደጋጋሚ ኢትዮጵያ በዴሞክራሲያዊ ሂደት ላይ እንዳለች ይናገራሉ፤ ይህ በአንተ አመለካከት እውነት ነው?"፤ "ከግንቦት 15 በፊት በተደረጉ ግድያዎች አገዛዙ የተቃዋሚዎች እጅ አለ ይላል፤ ይህን ታምናለህ?"፤ "በተለያዩ ጊዜያት ከሚደርሱ ፍንዳታዎች በስተጀርባ የትጥቅ ተቃዋሚ ቡድኖች እንዳሉ ይነገራል፤ ይህን ታምናለህ?" የሚሉ እና የመሳሰሉት ነበሩ።

ለነዚህ ጥያቄዎች በአማካይ 90% የሚሆኑት ተጠያቂዎች የአገዛዙን አቋም እንደማያምኑ ገልጸዋል። ብዙዎቹ አለ የሚባለው የኢኮኖሚ እድገት በነሱ ህይወት ላይ እንዳልተገለጠ እና በተለይም ባለፉት በርካታ አመታት እየተባባሰ የሄደው የዋጋ ንረት እነሱንም ሆነ የሚያውቋቸውን ሰዎች ህይወት ወደ ድህነት እንጂ ወደ መሻሻል እያሻገረ እንደሌለ ገልጸዋል። ዴሞክራሲያዊ ሂደትን በተመለከተ የአገዛዙ ባለስልጣናት የሚናገሩት በበርካቶች ዘንድ እንደ ቀልድ እንደሚወሰድም ታውቋል።

የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በሚመለከት ለተጠየቁት ጥያቄዎች በተለይ በዚ ጉዳይ ላይ አገዛዙ እንዲዋሽ እንጂ እውነቱን እንዲናገር እንደማይጠብቁ የሚገልጹ አመለካከቶች በብዙዎች ዘንድ ተንጸባርቀዋል። አሳሾቻችንን ያናገሩት አብዛኞቹ ተጠያቂዎች፣ እስከዛሬ የተነገሩትን ነገሮች ብቻ ሳይሆን ይህ አገዛዝ በማንኛውም ነገር ላይ በተለይ ከዚህ በኋላ እውነትን ይናገራል ብለው እንደማያምኑ ገልጸዋል። ብዙዎችም ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ በደርግ ጊዜ ከነበረው ጋር እንደሚያመሳስሉት ተናግረዋል።

ከሶስቱ ዜጎች ውስጥ ሁለቱ ከሚኖሩባቸው አካባቢዎች ጀምረው ወደ አዲስ አበባ ባቀኑ አውቶብሶች ላይ አብዛኞቹን ተጠያቂዎቻቸውን ያናገሩ ሲሆን፤ ሶስተኛው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በመንቀሳቀስ አሰሳውን አካሄዷል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org